# የአዲስ ግኝት ትምህርት ዓመት ካለንደር ትምህርት ቤቶች መመርያ መረጃና ስለ ተማሪ ብሕትዉነት/Privacy አመታዊ ማስታወቂያ

Annual Notice for Directory Information and Student Privacy for Innovative School Year Calendar Schools

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Rockville, Maryland, 20850
MCPS Regulation JOA-RA, Student Records

MCPS ቅጽ 281-13ISC
ጁላይ 2019
ከ2 ገጾች የመጀመርያው

**በቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶች እና ስለ "ብሕትዉነት" ህግ/ Privacy Act (FERPA)፣(20 U.S.C.§1232g፣34 CFR ክፍል 99) ያለዎትን መብቶች ስለማሳወቅ የተዘጋጀ አመታዊ መመርያ ለማየት ግልባጩን ገጽ ይመልከቱ**

ጠቋሚ መረጃ

ትምህርት ቤቶች የጠቋሚ መረጃዎችን ይፋ መዝገብ፣ ሆነር ሮል ሽልማቶች፣ እና ሌሎችንም በጋዜጣ ወይም የሞንትጎሞሪ ሕዝብ ት/ቤቶች (Montgomery County Public Schools (MCPS) ድረ-ገጽ ማስታወቂያዎች ለመሳሰሉት ዝርዝሮችን ይሰጣሉ። የተማሪው/ዋ ስም፣ አድራሻ፣ እና ስልክ ቁጥር ለወላጅ/የመምህራን ማህበራት (PTA) ሊሰጥ ይችላል። በእርስዎ በኩል ተቃውሞ ከሌለ በስተቀር ት/ቤቶች መረጃውን ያለርስዎ ፈቃድ ሊያስተላልፉት/ሊገልፁ ይችላሉ።

ጠቋሚ መረጃዎቹ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡- የተማሪ እና/ወይም የወላጅ ስም፣ አድራሻ፣ የኢ-ሜይል አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር፣ ተማሪ የተወለደ(ች)በት ቀን እና ቦታ፣ የሚያጠናው/የምታጠናው የትምህርት ዓይነት፣ የክፍል ደረጃ፣ በይፋ የሚታወቅ የተለያየ ዘርፍ እንቅስቃሴዎች እና ስፖርቶች ተሳትፎ፣ የተገኙ ድግሪዎች እና ሽልማቶች (ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡትን ጨምሮ)፣ በቅርብ ጊዜ የተማሩበት ትምህርት ቤት፣ የተከታተሉባቸው ቀናት፣ ፎቶ ግራፍ ወይም ሌላ ተመሣሣይ፣ የአትሌቲክ ቡድን አባሎች የሰውነት ክብደት እና ቁመት፣ እና ሌሎችም ተመሳሳይ መረጃዎች።

ትምህርት ቤትዎ የእርስዎን መረጃ እንዲገልጽ ካልፈለጉ ከዚህ በታች ያለውን ቅጽ ይሙሉና ይህን ማስታወሻ እስከ ጁላይ 12/2019 ለትምህርት ቤትዎ ይመልሱ። የዚህ ማስታወቂያ ተጨማሪ ቅጅዎች በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ት/ቤቶች (MCPS) ድረ-ገጽ ላይ በስፓንሽኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በቬትናሚኛ፣ በቻይንኛ፣ በኮሪያኛ እና በአማርኛ ቋንቋዎች ይገኛሉ።

ይህ ቅጽ በየአመቱ መሞላት አለበት።

ይህ ቅጽ እስከ ዓርብ፣ጁላይ 12/2019 ለትምህርት ቤትዎ ካልተመለሰ፣ማንነትዎን የማይገዳ መረጃ እንዲሰጥ ይስማማሉ ተብሎ ይወሰዳል።

በሌላ ጊዜ ሀሳብዎን መለወጥ ካስፈለገዎ ትምህርት ቤትዎን በቀጥታ ያግኙ።

ከ ጁላይ 12/2019 በኋላ ከተመዘገቡ ይህን ቅጽ በምዝገባ ወቅት ሊሞሉት ይችላሉ

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)
ለ 2019-2020 የትምህርት ዘመን ግላዊ ጠቋሚ መረጃ እንዳይሰጥ ስለመጠየቅ

ከሚከተሉት ምድቦች አንዱን ይምረጡ፡-

❏ እባክዎ ማንኛውንም ግላዊ መረጃ እንዳይገልጡ። (ፍቺውን እላይ ይመልከቱ)

❏ እባክዎ የሚከተለውን ጠቋሚ የመረጃ ክፍል ወይም ክፍሎችን አይስጡ። (በሚመለከተዉ ሁሉ ላይ ምልክት ያድርጉ)
❏ ስም ❏ የስልክ ቁጥር/ቁጥሮች ❏ ፎተግራፍ ❏ አድራሻ ❏ የተወለደ(ች)በት ቀን
❏ ኢ-ሜይል አድራሻ ❏ የወላጅ/የአሳዳጊ ስም ❏ የክፍል ደረጃ

እንዳይሰጥ ከተጠየቀዉና እላይ ከተጠቀሰው በስተቀር፡
❏ ለPTA መመርያ የሚሰጥ ❏ ለሆነር ሮል ህትመት የሚሰጥ ❏ ለአመታዊ-መጽሔት/yearbook የሚሰጥ ፎቶ

የተማሪ ስም ______________________________ የክፍል ደረጃ______ መታወቂያ ቁጥር __________

ትምህርት ቤት አንዱን ይምረጡ፡- -- Choose One -- ______________________________

የወላጅ/አሳዳጊ ወይም ዕድሜው/ዋ የሚፈቅድለት/ላት ተማሪ ፊርማ ______________________ ቀን_____/_____/______

ስለ ልጅዎ የተወሰኑ መረጃዎችን እንዳይሰጥ ካልገደቡ በስተቀር እያንዳንዱን ግላዊ መረጃ የወላጅ ፈቃድ ሳይጠይቁ የየእለት የስራ ክንውኖችን እና ተለምዷዊ/መደበኛ ስራቸውን እንዲያከናውኑ ለትምህርት ቤት ስርአት እና የአካባቢ ትምህርት ቤቶች አዎንታ እየሰጡ ነው።

## በ FERPA* መብቶችዎን ስለማሳወቅ የተገለጸ አመታዊ ማስታወቂያ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ እንደመሆንዎ መጠን የልጅዎን የትምህርት መረጃዎች በተመለከተ በቤተሰብ ትምህርታዊ እና ግላዊ መብቶች ህግ (Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA) አግባብነት ባላቸው የፌደራል ደንቦች እና በሜሪላንድ ስቴት ህግጋት (Code of Maryland Regulations (COMAR) 13A.08.02) መሠረት የተወሰኑ መብቶች አለዎት። እነዚህም መብቶች ከዚህ በታች ባጭሩ የተገለጹ ሲሆኑ የበለጠ ዝርዝር በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንብ የተማሪ ሪኮርዶች /JOA-RA፣ Student Records/ ድረ-ገጽ www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/joara.pdf ላይ ይገኛል።

1. የተማሪ መረጃዎችን ምልከታ፡- የልጅዎን የትምህርት መረጃዎች/ዘገባ የፅሁፍ ጥያቄ ት/ቤቱ ከተቀበለ ከ45 ቀኖች ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የመመርመርና የመገምገም መብት አለዎት። ትምህርት ቤቶች በተቻለ መጠን የጽሁፍ ጥያቄ በደረሳቸው በ10 ቀናት ውስጥ፤ የተማሪው/ዋን የማንነት/መለያ ግምገማ ወይም ከምደባ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ስብሰባ ከመደረጉ አስቀድሞ እንዲያከናውኑ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ግብ ነው። ትምህርት ቤቱ የልጅዎን መረጃዎች የሚያገኙበትን እና መዝገቦችን የሚያዩበትን ጊዜ እና ቦታ በማመቻቸት ያሳውቅዎታል። በዚህ ግምገማ ወቅት ርእሰ መምህሩ/ሯ/ ወይም ተወካይ ይኖራሉ።

2. የተማሪ ሪኮርዶች ማሻሻያዎች፡- የልጅዎ ዘገባዎች የተሳሳተ ወይም በአሳሳች ሁኔታ የተመዘገበ ነገር ካለ ወይም የልጅዎን ብሕትውነት/የግላዊ ማንነት/privacy/ መብቶች የሚጥሱ መስሎ ከታየዎ ት/ቤቱ ዘገባዎቹን እንዲያሻሽል የፅሁፍ ጥያቄ የማቅረብ መብት አለዎት። የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች MCPS ደንብ JOA-RA የተማሪ መዝገቦች እንደ አግባብነቱ ቅሬታ ማሰማትን ጨምሮ ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ አሰራሮችን ይዘረዝራል። በዚህ ደንብ መሰረት ውጤቶች ለድርድር አይቀርቡም።

3. የተማሪ መረጃዎችን ይፋ ማድረግ፡- በፌደራል ወይም የስቴት ህግ ያለፈቃድ እንዲገለጽ በተለይ የተፈቀደ እስካልሆነ ድረስ፤ በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) በግለሰብ ደረጃ የሚታይ መረጃ ከልጅዎ የትምህርት ዘገባዎች ይፋ ከመደረጉ በፊት የፅሁፍ ፈቃድ የመስጠት መብት አለዎት። ስለ መረጃ አሰጣጥ መመርያዎች እንዲሁም መረጃ እንዳይገለጽ ያለመስማማት ሁኔታን የሚገልጽ በዚህ ቅጽ በስተጀርባ ተጠቅሷል። በተጨማሪ ለመገንዘብ የሚያስፈልግዎት ነገር ህጋዊ የትምህርታዊ ሃላፊነት ላላቸው፣** የትምህርት ቤት የስራ ሃላፊዎች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ለመምህራን፣ ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች (መረጃ) ለመግለጽ ስምምነት እንደማያስፈልግ ያስተውሉ፡ እንደዚሁም የሚከተሉትን ሌሎች ስለ MCPS የሚሰሩ የስራ ሃላፊነታቸውን ለመወጣት መረጃ ማግኘት የሚያስፈልጋቸውን ጨምሮ፡- በትምህርት ቤት የጤና አገልግሎት ሠራተኞች፣ እና የጤና ባለሙያዎች፣ የት/ቤት የጥበቃ ሠራተኞች፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ አባላት፣ (Montgomery County Board of Education member)፣ ግለሰብ፣ ድርጅት፣ ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) እንዲሰሩ በኮንትራት የተቀጠሩ ካልሆነም በሞንትጎመሪ የሕዝብ ት/ቤቶች ቅጥር ሠራተኞች (ዓቃቤ ሕግ፣ ወይም ኦዲተሮች)፣ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ሌላ በፈቃደኝነት ሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች ውስጥ በኮሚቴ የሚያገለግል ወይም ሌሎች በትምህርት ዘርፍ በመርዳት የሚያገለግሉ አማካይነት።

- ጥያቄ ከቀረበ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) የትምህርት መረጃዎችን፣ ለሌሎች ት/ቤቶች፣ ለትምህርት ዲስትሪክት ወይም ከሁለተኛ ደረጃ በላይ ላሉ የትምህርት ተቋማት፣ የተማሪው መረጃ የተፈለገው ለትምህርት ምዝገባ ወይም ወደ ሌላ ት/ቤት የትምህርት ዲስትሪክት (ክፍለ ከተማ)፣ ወይም ሌላ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ለመዛወር ከሆነ ያለ ፈቃድ መረጃ መስጠት ይችላል። በተጨማሪ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) በህጋዊ መንገድ ከተማሪ መዝገቦች ላይ ግለሰብን ገላጭ የሆኑ መረጃዎችን ከእርስዎ የቅድሚያ የጽሁፍ ስምምነት ውጭ የተለዩ መንግስታዊ ድርጅቶችን፣ የጸደቁ የምርምር ፕሮጀክቶችን፣ የፍርድ ቤት ትእዛዝን ወይም ህጋዊ የፍርድ ቤት መጥሪያን፣ ወይም የጤና ወይም የደህንነት ድንገተኛ አደጋን ጨምሮ በFERPA ለተፈቀዱ ለሌሎች ምክንያቶች ሊገልጽ ይችላል።
  - ተጨማሪ መረጃ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መመሪያ JOA-RA፣የተማሪ ሪኮርዶች ድረ-ገጽ ወይም በእርስዎ የአካባቢ ትምህርት ቤት ይገኛል።

4. አቤቱታ ለዩ.ኤስ. የትምህርት መምርያ በFERPA ያለዎት መብቶች እንደተጣሱ ካመኑ እና ሁኔታውን/ጉዳዩን በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች MCPS የይግባኝ ደረጃዎች ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶች አጥጋቢ ካልሆኑ በዩ.ኤስ. የትምህርት መምሪያ የቤተሰብ ፖሊሲ አፈጻጸም ጽ/ቤት (the Family Policy Compliance Office)፣ 400 Maryland Avenue, SW, Washington, DC 20202-5920 ወይም በ1-800-USA-LEARN (1-800-872-5327) በመደወል አቤቱታ የማቅረብ መብት አለዎት።

* ብቃት ያላቸው ተማሪዎች መብቶች፡- እላይ የተገለጹት መብቶች 18 አመት ለሆነ/ች ወይም ድህረ ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ተቋም በመካፈል ላይ ላለ/ች ተማሪ ይሰራል፡ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ዕድሜ አሥራ ስምንት አመት የሚያሟላው/የምታሟላዋ ተማሪ የቅድሚያ ስምምነት ሳያስፈልጋቸው የልጃቸውን መረጃ/መዝገቦች ማግኘት/ማየት ይችላሉ።

**የትምህርት ቤት ባለስልጣናት ሙያዊ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የትምህርት መረጃዎችን/መዝገብን ለማየት/ለመገምገም ካስፈለጋቸው ህጋዊ የሆነ አጠቃላይ ሙያዊ ሃላፊነት አላቸው።